# ዜና ዕረፍት



**ጓድ ብርሃኑ ገብሬ ተሰማ (መንግሥቱ)**

መንግሥቱ በሚል የትግል ስም ይጠራ የነበረው ጓድ ብርሃኑ ገብሬ ተሰማ እሁድ ሚያዚያ 25 ቀን 2001 (May 3, 2009) በሚኖርበት በካርቱም ከተማ በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ጓድ ብርሃኑ ገብሬ የተወለደው በጎንደር ከተማ ቀበሌ 14 ሰበካ ገብርኤል አካባቢ ሲሆን በ1970/71 ዓ.ም. በደርግ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ የተነሳ ገና በለጋ ዕድሜው ከኢሕአፓ ሠራዊት ከኢሕአሠ ጋር ተቀላቅሎ ትግል ማካሄድ ጀመረ። ሠራዊቱን ከመቀላቀሉ በፊት በከተማ ውስጥ የኢሕ አወሊ አባል በመሆን የታገለ ሲሆን በሠራዊቱም ውስጥ በተለያዩ ኃይሎችና የተልእኮ ቡድኖች ውስጥ ተመድቦ ታግሏል። ወደ ሱዳን ከገባ በኋላም ከድርጅቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ቀጥሎ ህይወቱ እስካለፈበት ጊዜ ድረስ በተለያዩ ኃላፊነት ላይ በመመደብ ታግሎ ያታገለ ጓድ ነበር።

ጓድ ብርሃኑ ለሰው አዛኝና ሩህሩህ ከመሆኑ ሌላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደልና ስቃይ ዘወትር የሚያንገበግበው ቆራጥ ታጋይ ነበር። ዛሬ ጓድ ብርሃኑ በአካል ቢለየንም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረገው የትግል አስተዋጽ ህያው አድርጎት ይቆያል። ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም። ለባለቤቱና ለመላው ዘመዶቹ ጽናቱን ይስጣችሁ እንላለን።

ከትግል ጓዶቹ